# English Together

## Tanzania's app-based health insurance

*This is not a word-for-word transcript*

**ዘሩባቤል**
ሰላም፥ ስለአንድ ጉዳይ ወደምንወያይበትና ስለጉዳዩ ለማውራት የሚያስፈልገውን ቋንቋ ወደምናቀርብበት የEnglish Together ዝግጅት እንኳን በደህና መጡ። ዘሩባቤል እባላለሁ። አብረውኝቶም እና ፊል አሉ።

**Tom**
Hi, I'm Tom. Welcome to the programme, everyone!

**Phil**
And I'm Phil. Hello!

**ዘሩባቤል**
ዛሬ ተንቀሳቃሽ ስልኮች ምን ያህል ህይወታችንን በተሻለ ሁኔታ እየቀየሩት እንዳለ እናወራለን! ተንቀሳቃሽ ስልኮች የዕለት ተዕለት ህይወታችን ትልቅ አካል መሆናቸውን ስናስብ ጥያቄ አጫረብን፤ እ.አ.አ. በ2020 ከዓለማችን ህዝብ ውስጥ ምን ያህሉ የተንቀሳቃሽ ስልክ ተጠቃሚ ወይንም ተመዝጋቢ 'subscriber' ይሆናል?

ሀ) 30 በመቶ የሚጠጋ
ለ) 50 በመቶ የሚጠጋ
ሐ) 70 በመቶ የሚጠጋ

**Phil**
Well, here in London, everyone is on their phone all the time! I say 100%!

**Tom**
Yes, but our quiz is about the whole world's population, Phil, not just that in London.

**ዘሩባቤል**
አሁን ታንዛንያ ውስጥ የተንቀሳቃሽ ስልክ መተግበሪያ ከዚህ በፊት ለበርካቶች ከባድ የነበረውን የጤና መድህን ዋስትና 'health insurance' እንዲያገኙ በዛውም የጤና ክብካቤ 'healthcare' እንዲሰጣቸው ስለማስቻሉ የተሰራ የBBC Africa Business Report ዘገባን እንዳምጥ።

**News insert**
For millions of Tanzanians who live on low incomes, health insurance is a luxury they simply cannot afford. But, technology is beginning to change the landscape. Two years ago, mobile phone subscribers here in Tanzania rose by 25%. Now, technology analysts are convinced that mobile phones could indeed be key in changing people's lives in many aspects. With


© British Broadcasting Corporation 2018

only a basic feature phone, a customer can register for a policy and make payments for premium as low as a dollar a month.

**Phil**
You see, Tom? It's not just London. Mobile phone subscribers in Tanzania rose by 25% two years ago!

**Tom**
Yep, you're right, that is a huge increase. But what was more interesting to me in the story is the positive impact that mobile phones are having.

**ዘሩባቤል**
'To have a positive impact' አዎንታዊ ተፅዕኖ ማምጣት ማለት ነው። ተቃራኒው 'to have a negative impact' አሉታዊ ተፅዕኖ ነው። Yes, some good news about mobile phones!

**Tom**
And, it's nice to hear that mobile phones are actually having a positive impact on people's health. Often, we just hear the opposite.

**Phil**
We often hear the opposite because it's true! Mobile phones are having a negative impact on our health, on our relationship with others… They're often bringing about social change in negative ways.

**ዘሩባቤል**
'To bring about social change' ማኅበራዊ ለውጥ ማምጣት ማለት ነው። I agree that mobile phones can bring about social change in negative ways…

**Tom**
But don't you think giving people access to healthcare is an example of how mobile phones are bringing about social change in a positive way?

**ዘሩባቤል**
Before you answer Phil, let's go back to our quiz question from earlier: እ.ኤ.አ በ2020 ምን ያህሉ የዓለማችን ህዝብ ተንቀሳቃሽ ስልክ ተጠቃሚ ይሆናል?

  ሀ) 30 በመቶ የሚጠጋ
  ለ) 50 በመቶ የሚጠጋ
  ሐ) 70 በመቶ የሚጠጋ

statista.com ላይ በተቀመጡ የተለያዩ ግምቶች መሰረት መልሱ ሐ) 70 በመቶ አካባቢ ነው።
So, mobile phones are here to stay ከእኛ ጋር መቆየታቸው አይቀርም ማለት ነው።


© British Broadcasting Corporation 2018

**Phil**
Clearly! And, yes, of course I agree that access to healthcare should be a basic right.

**ዘሩባቤል**
'A basic right' መሰረታዊ መብት ማለት ነው። የጤና አገልግሎት ማግኘት ደግሞ አንዱ መሰረታዊ መብት ነው።

**Phil**
But, even though I agree that being able to see the doctor when you're ill should be a basic right, it's also a luxury that many people can't afford.

**ዘሩባቤል**
Very true. 'A luxury that people can't afford' ከሰዎች አቅም በላይ የሆነ ቅንጦት ማለት ነው።

**Tom**
Absolutely! Which is why I like this story so much. Now, it seems seeing a doctor doesn't have to be a luxury that people can't afford.

**Phil**
Because it's literally at their fingertips, you mean?

**Tom**
Exactly! Phil, did we just agree on something?

**Phil**
I think we did, yes.

**Tom**
Wow!

**ዘሩባቤል**
This news story really has had a positive impact!
እርስዎስ? የጤና ክብካቤ 'a basic right' መሆን አለበት ብለው ያስባሉ? ተንቀሳቃሽ ስልኮች በህይወታችን ላይ ሌላ አይነት 'positive impact' አላቸው ብለው ያስባሉ?
የዛሬውን ዝግጅታችንን አጠናቅቀን። ከመሰናበታችን በፊት፥ ስናወራባቸው የቆየናቸውን ቃላት አንዴ እንመልከት፤ ሁሉም ከማኅበራዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ናቸው። 'to have a positive impact' አዎንታዊ ተፅዕኖ ማምጣት ማለት ሲሆን፥ 'to bring about social change' ደግሞ ማኅበራዊ ለውጥ ማምጣት ነው። 'a basic right' መሠረታዊ መብት ማለት ነው፤ 'a luxury people cannot afford' ደግሞ ከሰዎች አቅም በላይ የሆነ ቅንጦት ማለት ነው። አብረውን ስለቆዩ እናመሰግናለን፤ ለተጨማሪ የEnglish Together ዝግጅት በሚቀጥለው ሳምንት ይጠብቁን።


© British Broadcasting Corporation 2018